# የኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት

**THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA**

His Imperial Highness Prince Ermias Sahle-Selassie Haile-Selassie
President


## <u>በአሲናራ ታስረው የነበሩ ታላላቅ የአገር ባለዉለታዎች ዝክረ-ታሪክ</u>

በጣልያን ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን፤ ትውልደ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች አነሳሽነት በአሲናራ ደሴት በፋሺስት መንግሥት ትዕዛዝ በግዞት ተይዘው የነበሩትን የአገራችን ታላላቅ ሰዎች ልዩ የመታሰብያ ዝግጅት እየተደረገ ነው። ፋሺስት አገራችንን ወሮ በነበረበት ግዜ ለአገዛዙ አደገኛ አስጊ ብሎ የፈራቸውን ሰዎች ከነቤተሰቦቻቸው በእስር ወደ ጣልያን አምጥቶ ማሰሩ የምናስታውሰው ታሪክ ነው። ከነዚህም መካከል የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴ የበኩር ልጅ የነበሩት ልዕልት ሮማነወርቅ ኃይለ ሥላሴ እና ሶስት ልጆቻቸው ይገኙ ነበር። ልዕልት ሮማነወርቅ እና ልጃቸው ልጅ ጌታቸው በየነ በእስር እያሉ አርፈው በቱሪን ከተማ ተቀብረው አፅማቸው አሁንም እዛው አርፏል። ንጉሠ ነገሥቱ ከተሰደዱ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ሆነው ሲመሩ የነበሩት ልውል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴም ለተወሰነ ግዜ በአሲናራ ታስረው ነበር። በጠቅላላው ወደ 400 ኢትዮጵያውያን በአሲናራ ታስረው ቆይተዋል። አብዛኞቹ ጣልያን ድል ከሆነ በኋላ ለአገራቸው ቢበቁም ታሪካቸው እና ገድላቸው እንደዚህ ጎልቶ የተከበረው ለመጀመርያ ግዜ በአሁኑ ዝግጅት ነው። ይህ ታሪክ እንዳይረሳ እና የነዚህ ታላላቅ የአገር ኩራት የነበሩ ሰዎች መስዋእትነት እንዲታወስ የሚደረግበት ይህ ልዩ ስነ ሥርዐት ሊመሰገን ይገባል። አዘጋጆቹም ለአገር ለወገን እና ለታሪክ ያላቸውን ፍቅር እና ክብር በማድነቅ የራሴንና የዘውድ ምክር ቤቱን ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ። በተለይ፣ ውጭ አገር ተወልደው ያደጉ ወጣት ኢትዮጵያዊያን ሃላፊነት ወስደው በአሲናራ ታስረው የነበሩ ታላላቅ የአገር ባለዉለታዎች ታሪክ እንዲዘከር ላሳዩት ቁርጠኝነትና ላበረከቱት አስተዋጽዖ ሁሉ በዘውድ ምክር ቤታችን ስም ምስጋናችንን እናቀርባለን።




***Princess Romanework in Italy with her children***



***Her children in Italy shortly before her death***

ውጣቱ ትውልድ አገርና ሕዝባችን ያለፈበትን ታሪክ በመማርና በመዘከር ለኢትዮጵያዊነት የተከፈለውን ውድ መስዋዕትነት እንዲገነዘብ ለማድረግ ይረዳዋል።

ኢትዮጵያን ፈጣሪ አምላክ ይጠብቃት። የአርበኛ አባቶቻችን እና እናቶቻችንም ነፍስ ይማር።

ልዑል ኤርሚያስ ሣሕለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ

የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት